# ትምህርት 45

1. እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ ልጅ ለመስጠት የገባውን ቃል ፈጽሞአል?

ሀ- አዎን።

2. ዘካርያስ አዳኙ እንደሚመጣና ሕዝቡን ከኃጢአት፣ ከሞትና ከሰይጣን ኃይል እንደሚያድናቸው በምን አወቀ?

ሀ- ዘካርያስ ያወቀው እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የገባውን የተስፋ ቃል ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ስላነበበ ነው።

3. የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ የሚሠራው ሥራ ምን ነበር?

ሀ- ዮሐንስ የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት በፊቱ ይሄዳል።

4. ዮሐንስ በፊቱ እየሄደ መንገዱን የሚያዘጋጅለት ይህ ጌታ ማን ነበር?

ሀ- እርሱ ኢየሱስ አዳኙ እግዚአብሔር ነበር።

5. የሚመጣው አዳኝ በማለዳ ፀሐይ የተመሰለው እንዴት ነው?

ሀ- የማለዳ ፀሐይ ለድቅድቅን ጨለማ ብርሃን እንደሚሰጥ ሁሉ፣ አዳኙም በሰይጣን ጨለማ ለተዋጠው ሕይወት ብርሃንን ይሰጣል።

6. በዓለም ላይ ስንት ፀሐዮች አሉ?

ሀ- አንድ ብቻ።

7. እግዚአብሔር ለመላክ ቃል የገባው አዳኝ ስንት ነበር?

ሀ- አንድ ብቻ።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ከዘራቸው አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገብቷል።

- አሁን ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ አዳኝ እንደሚልክ የገባላቸውን ቃል ፈጸመ።

ማቴዎስ 1፡1-2

1- የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ የሚከተለው ነው፤

2- አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብ ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፤

- ኢየሱስ የመጣው ከማን የዘር ሐረግ ነው?

- ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ የዘር ሐረግ ነው።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ቃል እንደገባው ኢየሱስ መምጣት ያለበት ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ የዘር ሐረግ ነው።

- እግዚአብሔር የገባውን ቃል ፈጽሞ አያፈርስም።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ቃሉን ይጠብቃል።

- ኢየሱስ የመጣው ከየትኛው የአይሁድ ንጉሥ የዘር ሐረግ ነበር?

- ከንጉሥ ዳዊት የዘር ሐረግ።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ቃል እንደገባው፥ ኢየሱስ መምጣት ያለበት ከንጉሥ ዳዊት ዘር ነው።

- እግዚአብሔር የገባውን ቃል ፈጽሞ አያፈርስም።
- እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተስፋ ቃሉን ይጠብቃል።

- የኢየሱስ ሌላው ስም ክርስቶስ ነበር።

- «ክርስቶስ» የሚለው የኢየሱስ ስም ትርጉም ምንድን ነው?

- «ክርስቶስ» ማለት ነቢይ፣ ካህንና ንጉሥ ማለት ነው።

- «ክርስቶስ» ማለት ነቢይ ማለት ነው።

- ኢየሱስ ታላቁ ነቢይ ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ተላከ።

- ኢየሱስ ታላቅ ነቢይ የሆነው እንዴት ነው?

- ኢየሱስ ታላቁን መልእክት፥ የእግዚአብሔር የራሱን ቃል ስለሚናገር ነው።

- ኢየሱስ ታላቁን መልእክት የሚናገር ታላቅ ነቢይ እንዲሆን በእግዚአብሔር ተላከ።

- «ክርስቶስ» ማለት ደግሞ ካህን ማለትም ነው።

- ኢየሱስ ታላቁ ካህን እንዲሆን በእግዚአብሔር ተላከ።

- ኢየሱስ ታላቅ ካህን የሆነው እንዴት ነው?
- ኢየሱስ ታላቁን መሥዋዕት ስለሚያቀርብ ነው።

- ኢየሱስ ታላቁን መሥዋዕት የሚያቀርብ ታላቅ ካህን እንዲሆን በእግዚአብሔር ተላከ።

- «ክርስቶስ» ማለት ደግሞ ንጉሥ ማለትም ነው።

- ኢየሱስ ከዳዊት የዘር ሐረግ የመጣ ንጉሥ ሆኖ እንዲነግሥ በእግዚአብሔር ተላከ።

- ኢየሱስ ታላቁ ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር ተላከ።

- ኢየሱስ ታላቅ ንጉስ የሆነው እንዴት ነው?
- ምክንያቱም የኢየሱስ መንግስት ዘላለማዊ ስለሆነ ነው።

- ኢየሱስ ለዘላለም የሚገዛ ታላቅ ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር ተላከ።

- አዳኝ እንዲሆን በእግዚአብሔር ቃል የተገባው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር።

- ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ለማዳን በእግዚአብሔር ቃል የተገባው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር አዳኙን እንደምትወልድ እንዲነገራት መልአኩን ወደ ማርያም ለከ።

- ይሁን እንጂ ማርያም ዮሴፍ ለተባለ ሰው ሚስት እንድትሆን ታጭታ ነበር።

- ችግሩ ይህ ነበር፡
- ማርያም ድንግልና ለዮሴፍ የታጨች ሆና ሳለች፣ አርግዛ ተገኘች።

- ዮሴፍ ማርያምን ስላላገባት ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸመም።

- ማርያም በማርገዟ ዮሴፍ ምን አሰበ?

- ዮሴፍ ማርያም ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደፈጸመች አሰበ።

- ስለዚህ፣ ዮሴፍ ማርያምን ሊተዋት አሰበ።

ማቴዎስ 1፡18-19

18- የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ እንዲህ ነው፤ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳይገናኙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።

19- እጮኛዋ ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ስለ ነበርና ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት ስላልፈለገ በስውር ሊተዋት ወሰነ።

- ማርያም ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽማለች?
- አልፈጸመችም።

- ታዲያ ማርያም እንዴት አረገዘች?

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተአምር ስለሠራ ማርያም አረገዘች።

- በማርያም ማሕፀን ውስጥ የነበረው ሕፃን አዳኙ እግዚአብሔር ነበር።

- እግዚአብሔር ዮሴፍ ማርያምን እንዲተዋት አልፈለገም።

- ስለሆነም እግዚአብሔር በሕልም ከዮሴፍ ጋር እንዲነጋገር መልአኩን ላከ።

ማቴዎስ 1፡20-21

20- በዚህ ሐሳብ ሳለ፣ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ተገለጠለት፤ እንዲህም አለው፤ «የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፤ እጮኛህን ማርያምን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ፤ የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነውና።

21- ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም ኢየሱስ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና።»

- መልአኩ ዮሴፍን በሕልም ምን አለው?

- መልአኩ ማርያም የጸነሰችው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተአምር በመስራቱ መሆኑን ተናገረ።

- መልአኩ የማርያም ልጅ አዳኙ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ተናገረ።

- መልአኩ ዮሴፍ ማርያምን ወደ ቤቱ እንዲወስዳት ነገረው።

- መልአኩ ዮሴፍ ለማርያም ልጅ ኢየሱስ የሚል ስም እንዲያወጣለት ነገረው።

- ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን በዚህ ዓለም ውስጥ ተወለደ።

- ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት ኃይል ለማዳን መጣ።

- ኢየሱስ ሰዎችን ከሞት ኃይል ለማዳን መጣ።

- ኢየሱስ ሰዎችን ከሰይጣን ኃይል ለማዳን መጣ።

ማቴዎስ 1፡22-23

22- ጌታ በነቢዩ (በኢሳይያስ) እንዲህ ሲል የተናገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ፤

23- «እነሆ፣ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤ ትርጉሙም፣ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ማለት ነው።

- ነቢያት አዳኙ ከድንግል እንደሚወለድ ተናገሩ።

- እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ከረጅም ዘመናት በፊት ቃል በገባው መሰረት፣ ኢየሱስ ከድንግል ተወለደ።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ብዙ ስሞች አሉት።

- ሌላው የኢየሱስ ስም አማኑኤል ነበር።

- «አማኑኤል» የሚለው ስም ትርጉም ምንድን ነው?

- አማኑኤል ማለት «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ማለት ነው።

- ኢየሱስ አማኑኤል ተብሎ የተጠራው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ከሰዎች ጋር ሊኖር የመጣ አዳኙ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ማርያም የወለደችው ልጅ ኢየሱስ፣ አዳኙ እግዚአብሔር፣ ከሰዎች ጋር ይኖር ዘንድ ከሰማይ መጣ።

- ዮሴፍ ከሕልሙ ከነቃ በኋላ ምን አደረገ?

ማቴዎስ 1፡24-25

24- ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቃ፤ ከዚያም የጌታ መልአክ እንዳዘዘው ማርያምን ወደ ቤቱ ወሰዳት።

25- ይሁን እንጂ የበኲር ልጇን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ የተወለደውንም ሕፃን፣ «ኢየሱስ» ብሎ ጠራው።

- ዮሴፍ እግዚአብሔር በመልአኩ አማካይነት የተናገረውን ታዘዘ።

- ዮሴፍ ማርያምን ሚስቱ እንድትሆን ወደ ቤቱ ወሰዳት።

- ይሁን እንጂ ማርያም ልጇን እስክትወልድ ድረስ ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸመም።

- በሚቀጥለው ትምህርት ስለ ኢየሱስ መወለድ እንማራለን።